በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.241998
**ጥቅምት 01/2016 ዓ.ም**

**ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)**

**እንዳሻው አዳነ**

**ተሾመ ሽፈራው**

**መላኩ ካሳዬ**

**ነፃነት ተገኝ**

**አመልካች፡ ወ/ሮ የጅማወርቅ ማሞ -- ጠበቃ አቶ ደሳለኝ ደመቀ ቀረቡ**

**ተጠሪ፡ አቶ ነገሱ ኩምሳ --- ቀርበዋል፡፡**

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ጋብቻ በፍቺ ቀሪ መሆንን ተከትሎ የቀረበ የባልና ሚስት የንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/420201 ላይ ጥር 09/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ቀሪ መሆኑን ተከትሎ የአሁን አመልካች ባቀረቡት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ አመልካች ባቀረቡት የጋራ ንብረት ዝርዝር ላይ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘው መሰረት ተገቢ ነው ያሉትን መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ ከዚሁ ጋርም የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ሆኖ እያለ አመልካች ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ በሻኪሶ ከተማ አስተዳደር በንቲ አርባ ቀበሌ ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 207 የሆነው መኖሪያ ቤት የጋራ ንብረት መሆኑን ጠቅሰው ክፍፍል እንዲደረግበት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የተጠቀሰው

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቤት ከወላጆቻቸው በውርስ ያገኙት እንጂ የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት አለመሆኑን ጠቅሰው ከክፍፍሉ ሊወጣ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም በፍቺ ውጤቱ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረና ማስረጃ ከሰማ በኃላ ክርክር የተነሳበት ቤት በውርስ የተገኘ በመሆኑ የአመልካች የግል ሀብት እንጂ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት አይደለም በሚል በተጠሪ የቀረበውን የክፍፍል ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

ተጠሪ ይህንን ውሳኔ እና ሌሎች ንብረቶችንም አስምልክቶ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ ግራ ቀኙ የሌሎች ወራሾችን ድርሻ በመክፈል ያስቀሩት በመሆኑ የጋራ ነው በማለት እና ሌሎች ንብረቶችንም በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በተራቸው በውርስ ያገኙት ቤት የጋራ ነው በሚል መወሰኑን በመቃወም የይግባኝ አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች በውርስ ያገኙት ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በትዳር ውስጥ በቤቱ ላይ ከወጣው ወጪ ውስጥ የአሁን ተጠሪ ግማሹ ከሚከፈላቸው በስተቀር ቤቱ የጋራ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት በሌሎች ንብረቶች ላይ የወረዳው ፍ/ቤት በድጋሚ አጣርቶ እንዲወሰን በነጥብ መልሷል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ ቤቱ የጋራ አይደለም በሚል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሰበር ችሎቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ቤቱ በጋብቻ ውስጥ በውርስ የተገኘ ቢሆንም የግራ ቀኙ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ወቅት በቤቱ ላይ የወጣው ወጪ ዋጋ ከነባር ቤቱ ዋጋ እጥፍ በላይ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ በቤቱ ላይ የወጣውን ወጪ ብቻ እንዲካፈሉ መወሰኑ ከህግ አግባብ ውጭ ነው በማለት ከዚህ አንፃር የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሯል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 06/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የቤቱ ግምት ሳይታወቅ፣ በቤቱ ላይ የተደረገው ለውጥ /እድሳት/ ሳይጣራ መሰረታዊ ለውጥ ተደርጎበታል በሚል ምክንያት ቤቱ የጋራ ነው ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ግራ ቀኙ በጋብቻ ፀንተው በነበሩበት ወቅት አመልካች በውርስ ያገኙት መሆኑን፣ ይኸው ቤት ሲገኝም ባልና ሚስቱ ከቤቱ ላይ የውርስ ድርሻ ለነበራቸው ሌሎች ወራሾች የድርሻቸው ከጋራ ሃብታቸው ላይ የከፈሉ መሆኑን፣ እንዲሁም በጋብቻ ውስጥ በዚሁ ቤት ላይ የተደረገው መሻሻል እና በአጠቃላይ ቤቱ ላይ የወጣው ወጪ በውርስ ከተገኘው ዋናው ቤት ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ከእጥፍ በላይ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ያሳያል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱም ለውሳኔው መሰረት ያደረገው እነዚህኑ በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ስለመሆኑ በውሳኔው በግልጽ አመላክቷል፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

እንግዲህ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና ህገ መንግስቱን ተከትሎ በታወጀው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ማናቸውንም የመጨረሻ ዉሳኔዎችን መርምሮ ማረም ነው፡፡ መሰረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነም በአዋጁ የትርጉም ክፍል በአንቀጽ 2(4) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ችሎቱ ይህንን ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርጉ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋናነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡

በህግ ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ማስረጃን በመመርመር እና በመመዘን የሚደርሱበት ድምዳሜ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የበታች ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸውን ማስረጃዎችን ይዘት በአግባቡ ሳይመለከቱ ሲቀሩ፤ ወይም በማስረጃ የተረጋገጠው እና ፍርድ ቤቶቹ የደረሰበት ድምዳሜ የተለያዩ ሆነው ሲገኙ አልያም በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀሙት መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት መኖሩ ሲረጋገጥ እንደሆነ በዚሁ ችሎት በተደጋጋሚ የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል የሰበር አቤቱ የቀረበበት የመጨረሻ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ከሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዮቹም ለህዝብ ጥቅም ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10(1(ሐ) እና (መ))) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

ከዚህ አኳያ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10(1(ሐ) እና (መ)) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/420201 ላይ ጥር 09/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም